11ኛ ዓመት ቁጥር 18
11th Year No. 18

ባህር ዳር ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ/ም
Bahir Dar May 29,2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር ----
Unit price -----

ማውጫ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ/ም	CONTENT Proclamation No. 133/2006
የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ	The Revised Amhara National Regional State Rural Land Administration and Use Proclamation

አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ/ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የገጠር መሬትን ባግባቡና በእንክብካቤ በመጠቀም ለምነቱን ጠብቆ ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻል አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ወስኖ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

በብሔራዊ ክልሉና በፌዴራሉ ሕገጋተ መንግስታት የተረጋገጠውን የአርሶ አደሮችና የከፊል አርብቶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከይዞታ ያለመነቀል መብት በተሟላ ሁኔታ በክልሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፤

Proclamation No. 133/2006

A proclamation issued to provide for the Revised Rural Land Administration and Use of the Amhara National Regional State

WHEREAS, it is found necessary to determine and provide the rural land administration and use to maintain its fertility and to be able to transfer to the next generation by using it properly and carefully;

WHEREAS, it is understood that to create conducive situation in the region to fully make practical the rights of farmers and semi-pastorals to get and use land freely and not be displaced from it as ensured in the Federal and National Regional Constitutions;

መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ለክልሎች በተሰጠው ስልጣን መሠረት አርሶ አደሩ፣ ባለሀብቱና አግባብ ያላቸው ድርጅቶች መሬትን በአግባቡ በማልማት በመጠቀምና በመጠበቅ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማጠናከርና ከመንግሥት የልማት ዓላማዎች ጋር እንዲቀናጅ ለማድረግ የሚያስችልና በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ቀርጾ በሥራ ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ በማመን፤

በሥራ ላይ ያለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የአርሶ አደሮችን መሠረታዊ መብቶች በዝርዝር በሚያካትት አግባብ ያላቸውን የፌዴራል መንግስት ሕጐች ተፈፃሚነት በሚያረጋግጥ አኳኋን መሻሻል ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

የክልሉ ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ እና በፌዴራሉ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ዓ.ም. አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

WHEREAS, it is believed that to design and implement a system based on the objective realities of the region pursuant to the power vested to regions by the Federal Constitution to administer the land and the natural resources and strengthen the farmer, the investor and appropiate organizations in their participations to use land maintaining it properly, use and keep, and to coordinate it with the development objectives of the government;

WHEREAS, it is found necessary to revise the existing Rural Land Administration and Use Proclamation to incorporate,in detail, the basic rights of farmers, and ensure the implemntation and inclusion of the laws of the federal government;

NOW, THEREFORE, the Regional Council in accordance with the powers vested on it under sub article 3(1) of Article 49 of the Revised Constitution of National Region and Sub-article 1 of Article 17 of the Federal Rural Land Administration and Use Proclamation No. 456/2005, hereby issues this proclamation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "አርሶ አደር" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የግብርና ሥራ የሆነ ማናቸውም ሰው ሲሆን ከፊል አርብቶ አደሮችን ይጨምራል።

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Proclamation can be cited as "The Revised Rural Land Administration and Use Determination Proclamation No. 133/2006".

2. Definition

Unless the context requires, other wise, in this proclamation.

1. "Farmer" means any person whose regular or steady earning is based on agricultural activities and includes semi-pastorilists.

2 “ባለሥልጣን” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣን ነው።

3 "ልጅ" ማለት በሥጋ የተወለደ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ማለት ነው።

4. “ተጧሪ” ማለት በዕድሜ መግፋት፣ በበሽታ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ሳቢያ በራሱ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የተሳነውና ለመተዳደሪያው የሌሎችን ሰዎች ዕርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው።

5. “የወል ይዞታ” ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝና የአካባቢው ነዋሪዎች በህብረት የሚጠቀሙበት መሬት ሲሆን ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች የዋለ መሬት ነው።

6. “የቤተሰብ አባል” ማለት ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው የይዞታ ባለመብቱን አርሶ አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው።

7. “የመንግሥት ይዞታ” ማለት ለአገርና ለአካባቢ ልማትና እድገት ተብሎ በመንግሥት ይዞታነት በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተያዘ መሬት ሲሆን ጥብቅ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንሰሳት መጠለያዎችን፣ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን፣ ፖርኮችንና በሃይቆችም ሆነ በወንዞች አካባቢ የሚገኙ ሥፍራዎችን ያጠቃልላል።

8. "የይዞታ መብት" ማለት ማንኛውም አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር ወይም በአዋጁ መብት የተሰጠው ሌላ ማናቸውም አካል በዚህ አዋጅ መሰረት የተረጋገጡለትን የመሬት ባለይዞታ የመሆን፣ በመሬቱ ላይ ንብረት የማፍራት፣ ያፈራውን ንብረት የማስተላለፍ፣ ከይዞታ መሬቱ ያለመነቀል፣ መሬቱን ለግብርናና ለተፈጥሮ ሃብት ልማትም ሆነ ለሌሎች ተግባራት የማዋል፣ የመጠቀም፣ መሬቱን የማከራየት፣ የማውረስ፣ በስጦታ የማስተላለፍና የመሳሰሉትን መብቶች የሚያጠቃልል ነው።

2. “Authority” means the Amhara National Regional State Environmental Protection, Land Administration and Use Authority.

3. “Child” means natural or adopted child.

4. “Pensioned” means any person who unable to engage in work that creates income by himself and seeks others help for his livelihood due to senility, disease, disability or other related reasons.

5. “Communal Holding” means rural land which is out of the ownership of the government or private holding and used by the local people in common for grazing, forestry and other social services.

6. “Family Member” means any person who permanently lives with the land holder sharing the livelihood of the later and who doesn’t have his own regular income.

7. “State Holding” means rural land demarked and held by Federal or Regional Government for country and area development and growth, and it includes forest lands, wild life sanctuaries, mining lands and parks as well as lands around lakes and rivers.

8. “ Holding Right” means a right of any farmer or semi pastoral or any other body vested with rights on it in accordance with this proclamation to be the holder of a land, to create all asset on the land, to transfer an asset he created, not to be displaced from his holding, to use his land for agricultural and natural resource developments and other activities, to rent a land, to bequeath same to transfer it as a gift and includes the likes.

9. “የግል ይዞታ” ማለት በማንኛውም አርሶ አደር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የመጠቀም መብት በተሰጠው ሌላ አካል እጅ ሆኖና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ወጥቶለት በግል ይዞታ ሥር የሚገኝ መሬት ነው፡፡

9. “Private Holding” means a land possessed by any farmer or other body vested with right to use it and existing under private holding having a certificate.

10. “የጋራ ይዞታ” ማለት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ መሬት ላይ ያልተከፋፈለ የይዞታ ባለመብቶች ሆነው መሬቱን ሳይከፋፈሉ ከዚሁ ከመሬቱ የሚገኘውን ጥቅም እየተጋሩ የሚጠቀሙበት መሬት ነው፡፡

10. “Common Holding” means holding of land by two or more persons in common having the holding right, and use without division, by sharing the out put from the land.

11. “የቀበሌ ነዋሪ” ማለት መደበኛ መቀመጫውን በአንድ ቀበሌ አድርጎ መሠረታዊ አገልግሎቶቹንና ማህበራዊ ጥቅሞቹን በዚያው ቀበሌ ውስጥ የሚያገኝ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

11. “ Kebele resident” means any person who resides regularly in one kebele and earns the basic services and social benefits in the same.

12. “የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ” ማለት በፊዚካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎች መሠረት የመሬት መጐሣቆልና የአካባቢ ብክለት ሣይደርስበት መሬት ሊሰጥ ከሚችላቸው አማራጭ ጥቅሞች የተሻለው ተመርጦ ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓት ሲሆን ስልታዊና የአካባቢ ልማት እቅዶችን ያጠቃልላል፡፡

12. “Land Use Plan” means the system of making practical the better chosen alternatives to use land without degradation and environmental pollution based on physical, economical and social information and includes strategic and area development plans.

13. “የመሬት ተጠቃሚ” ማለት የገጠር መሬትን የመገልገልና በምርቱ የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፡፡

13. “Land User” means any person vested with power to use the rural land and its production.

14. “ሰው”ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

14. “Person” means natural or legal person.

15. "የሕዝብ አገልግሎት" ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ እንደ መንግስት መ/ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና አገልግሎት፣ የገበያ አገልግሎት፣ መንገድ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የወታደር ካምፕ የመሳሰሉትና በክልሉ መንግሥት ለሕዝብ እድገት ይጠቅማሉ ተብለው በገጠር መሬት ላይ እንዲፈፀሙ የሚወሰኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

15. “Public Service” means a service given to the public directly or indirectly,such as government office, school, health service, market service, road, religious institutions, military camps, and the likes, and includes activities assumed important to the development of people by the Regional Government and to be implemented on the rural land.

16. “ሌላ ንብረት” ማለት ከመሬት በስተቀር ማናቸውም ሌላ ንብረት ነው።

17. “የመጠቀም መብት” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በመሬት የመገልገልና የሚገኘውን ምርት የመጠቀም መብት ነው።

18. "መሬት ማስለቀቅ" ማለት የገጠርን መሬት ለሕዝብ አገልግሎት ሲባል በመንግስት አካላት፣ በግል ባለሃብቶች፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም በሌሎች አካላት ልማት እንዲካሄድበት ሥልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል ወሣኔ መሰረት በቅድሚያ ካሣ ከፍሎ ከመሬቱ ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ መውሰድ ማለት ነው።

19. "የመሬት ባለይዞታ" ማለት በአንድ የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት ያለው ግለሰብ፣ የሰዎች ስብስብ ወይም ሕብረተሰብ፣ የመንግስት አካል፣ ማህበራዊ ተቋም ወይም ሌላ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው።

20. "የመሬት ምዝገባ" ማለት የገጠር መሬትን በተመለከተ የሚገኝበትን ቦታ፣ ስፋቱን፣ አዋሣኞቹን፣ የለምነቱን ደረጃና የባለይዞታውን ማንነት ጨምሮ የተሟላ መረጃ በመዝግብ ላይ የማስፈር ተግባር ነው።

21. "አነስተኛ የይዞታ መጠን" ማለት ሥልጣን በተሰጠው አካል አማካኝነት ምርት የመስጠት አቅሙ የአንድን አርሶ አደር፣ ወይም ከፊል አርብቶ አደር የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ ለእንስሳት ግጦሽ፣ ለቤት መስሪያና ለጓሮ አትክልት ልማት በቂ ነው ተብሎ በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የመሬት መጠን ነው።

22. "አነስተኛ የማሣ መጠን" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰንና ለአንድ ሰው በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የአንድ ማሣ ስፋት ነው።

16. “Another property” means any property other than the land.

17. “Use Right” means using the land and its production, pursuant to this Proclamation.

18. “Expropriating from land holding” means taking the rural land from the holder or user for the sake of public interest paying compensation in advance by government bodies, private investors, cooperative societies, or other bodies to undertake development activities by the decision of government body vested with power.

19. “Land holder” means an individual, group of people or community, government body, social institution or other body with the legal personality having a possession right over a rural land.

20. “Land registration” means an activity of registering the detailed information about location, area, boundaries, fertility grade, and the identity of the holder on the book concerning the rural land.

21. “Minimum Holding Size” means the least piece of land given to farmers or semi-pastoralists to ensure food security, animal grazing, house construction, and horticultural development, as a holding land, assuming it satisfactory.

22. “Small Plot Size” means the minimum plot of land to be given to a person in holding and shall be determined by a regulation to be issued pursuant to this Proclamation.

23. "የገጠር መሬት አስተዳደር" ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የመሬት አጠቃቀም እቅድ የሚተገበርበት፣ በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበትና የማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መብቶችና ግዴታዎች የሚተገበሩበት፣ እንዲሁም የባለይዞታዎች ማሳዎችን፣ የግጦሽ መሬትን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲዳረሱ የሚደረግበት ሂደት ነው::

23. “Rural Land Administration” means a process whereby rural land holding security is provided, land use planning is implemented, desputes between rural land holders are resolved, and the rights and obligations of any rural land holder are enforced, as well as information on farm plots and grazing land of holders are gathered, analyzed and supplied to users.

24. "የገጠር መሬት "ማለት ሥልጣን ያለው አካል ከተማ ብሎ ከከለለው ውጭ የሚገኝ መሬት ነው::

24. “Rural Land” means any land found out of town which is delineated by a body vested with power.

25. "ኪራይ" ማለት አንድ አርሶ አደር በዚህ አዋጅ መሰረት ያገኘውን የመሬት ይዞታ ለሌላ ሰው ለተወሰነ የጊዜ ገደብ በውል ሰጥቶ የአይነት ወይም የገንዘብ ጥቅም እየተቀበለ አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚያደርግበት ስሪት ነው::

25. “Rent” means a system by which a farmer causes the use of his land, which he gets it pursuant to this proclamation, for the service of another person securing benefits in kind or cash for a limited period of time in contract.

26. "ሊዝ" ማለት ማንኛውም ባለሃብት የገጠርን መሬት ለተወሰነ አገልግሎት ከመንግስት የሚወስድበት አሠራር ሲሆን አግባብ ባለው ህግ እንደተተረጐመው የመጠቀምና የዕዳ ዋስትና አድርጐ እስከ ማስያዝ የሚደርሱ መብቶች የሚካተቱበት ነው::

26. “Lease” means a system by which any investor takes a rural land from government for a limited period of time, and, as it is interpreted in relevant law, the right to use the land includes the holding of same for debt as suretyship.

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ ለሴት ፆታም እኩል ተፈፃሚ ይሆናል::

3. Gender Reference

The provisions of this proclamation set out in the masculine gender shall also equally apply to feminine gender.

4. የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልል በሚገኝ ማንኛውም የገጠር መሬት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

4. Scope of Application

1. This proclamation shall apply to any rural land found in Amhara National Region.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ለደን፣ ለዱር አራዊት ጥበቃ፣ ለብዝሃ ሕይወት ሀብትነት፣ ለተፈጥሮ ሀብትና ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለማዕድን ልማትና ለመሳሰሉት የተከለሉ መሬቶችን መንከባከብና ማልማትን በተመለከተ የወጡ ልዩ ህጐች እንደየተደነገጉባቸው መስኮች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል::

ክፍል ሁለት

የመሬት ይዞታ መብት

5. መርህ

1. የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ነው:: በመሆኑም የመሬት ይዞታን በሽያጭም ሆነ በሌላ ንብረት በመለወጥ ለሌላ ማስተላለፍ አይቻልም::

2. በክልሉ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም አርሶ አደር በፆታም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት መሬት በይዞታ የማግኘት እኩል መብት አለው::

3. በክልሉ ውስጥ የአርሶ አደሮች የገጠር መሬት ይዞታ መብት የጊዜ ገደብ የለውም::

4. የመሬት አስተዳደር ሥርዓት በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ይሆናል::

5. የመሬት አጠቃቀም በእቅድና አካባቢን በመንከባከብ ላይ አተኩሮ የሚፈፀም ይሆናል ::

6. የመሬት ድልድል በሚካሄድበት ጊዜ ለሴቶች፣ ለአቅመ ደካሞችና ለወላጅ አልባ ሕፃናት ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚያደርግ አሠራር ተፈፃሚ ይሆናል::

2. Notwithstanding the provision stated under sub Article 1 of this Article, special laws shall continue on application, as the fields they had been stipulated, concerning the delineated lands for forestry, wild life protection, bio-diversity resources, natural resource and environmental protection, mines developments and the likes.

Part Two

Right to Hold Land

5. Principle

1. The right to ownership of land is vested in the state and the public. Hence, it is impossible to transfer the land holding to other in sale or in exchange by an other property.

2. Any farmer residing in the region shall, despite gender or any other reasons of deference, have equal right to get land in holding.

3. The holding right of rural land of farmers, in the region, shall not have time limit.

4. The system of land administration shall be based on public participation.

5. The land use may be applicable based on plan and considering environmental protection.

6. The working system that gives priority to women, disables and orphan children shall be executed during the time of land distribution.

7. ተዳፋትነቱ 60 በመቶና ከዚያ በላይ የሆነ ማናቸውም የገጠር መሬት ለደን፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለእንስሣት መኖ ልማት ወይም ለመሣሰሉት ተግባራት ካልሆነ በስተቀር ለእርሻም ሆነ ለልቅ ግጦሽ እንዲውል አይደረግም:: ሆኖም ይህ ድንጋጌ በእንዲህ ያለው የገጠር መሬት ላይ አስቀድመው የሚገኙ ባለይዞታዎች የአካባቢ ጥበቃንና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በማይጐዳ አኳኋን መሬቱን ለተጠቀሰው አገልግሎት በባለሙያ ምክር እየተረዱ እንዳይጠቀሙበት የማገድ ውጤት አይኖረውም::

8. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ካልሆነ በስተቀር የገጠር መሬት እንዲለቀቅ አይደረግም::

6. መሬት የማግኘት መብት

1. ማንኛውም እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በክልሉ ውስጥ በግብርና ሥራ ለመተዳደር የሚፈልግ ሰው የመሬት ይዞታ በነፃ የማግኘት መብት አለው::

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም እድሜአቸው 18 ዓመት ያልሞላቸውና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት የሚተዳደሩበት መሬት በሞግዚታቸው ወይም በወኪላቸው አማካይነት ሊሰጣቸው ይችላል::

3. የግል ባለሀብቶች የሚጠቀሙበት መሬት ከመንግስት በኪራይ ወይም ከማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ጋር በሚደረግ ስምምነት የማግኘት መብት አላቸው::

7. Any rural land, 60 per cent and above sloppy shall not be used for farming and free grazing other than forestry, pernial plants, development of forage for animals, and other similar activities. However, this provisions shall have not effect on the same rural land priory seized by the land holders who use it in that it doesn't damage the environmental protection and sustainable natural resource care being helped by the advice of the professional.

8. Without prejudice to provision of sub-Article 2 of Article 8 of this proclamation, the rural land shall not be expropriated unless to use it for public service.

6. The Right to Acquire Land

1. Any Person,who is18 years and above, residing in the region and in need of engaging in agricultural activity shall have a right to freely acquire holding land.

2. Notwithstanding the provision stated under sub-article 1 herein above, children who lost their parents and are under 18 years may get a land through their guardian or representatives.

3. Private investors shall have a right to acquire land, to use on, by rent from the government or from any other rural land holder on the agreement to be made.

4. በክልሉ ውስጥ ሥራቸውን የሚያካሂዱ መንግስታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የብዙሃን ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ለገንዘብ ትርፍ እስካልሆነ ድረስ የአርሶ አደሮችን መሬት የማግኘት መብት በማይጎዳር ሁኔታ የሚጠቀሙበት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አላቸው።

7. መሬት በይዞታ የሚገኝባቸው ሁኔታዎችና የይዞታ ጣሪያ

1. በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚከተለው አኳኋን መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አለው፡-

   ሀ. በመደበኛነት በሚኖርበት ወይም መኖር በሚፈልግበት ቀበሌ መሬትን ከሚያስተዳድረው አካል በድልድል፣

   ለ. ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በማናቸውም የክልሉ አካባቢ በውርስ ወይም በስጦታ።

2. ለአንድ ሰው በይዞታ የሚሰጠው መሬት ጠቅላላ ስፋት ጣሪያ፣መሬትን በይዞታም ሆነ በኪራይ ለማግኘት ጥያቄ የሚቀርብበትም ሆነ ምላሽ የሚያገኝበት ሥርዓት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ወደፊት በሚወጣ ደንብ የሚደነገግ ይሆናል።

8. ስለመሬት ሽግሽግ

1. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በየትኛውም የክልሉ አካባቢ የመሬት ሽግሽግም ሆነ ክፍፍል አይካሄድም።

4 Governmental offices and organizations, non-governmental organizations, mass organizations and religions institutions, carrying out their works in the region, shall, where the work is for non-profit making, have a right to acquire land they use on in a condition that it does not contravene the land holding of farmers.

7. Conditions of Acquiring Land Holding and Limitation

1. Any Person residing in the region and engaged or wants to be engaged in agricultural works shall have a right to acquire land in holding in the following manner:

   a) By distribution from the keble administering the land in which he regularly resides or wants to reside,

   b) By bequeath or gift, the detail to be determined by a regulation to be issued to implement this proclamation, any where in the region.

2. The total area of land to be given to a person in holding and a procedure to apply for as well as get reply to acquire land in holding or in rent shall be provided in the regulation to be issued to implement this proclamation.

8. Land Re-distribution

1. In any part of the region, land distribution and allotment shall not be carried out since the coming into force of this proclamation.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ቢያንስ ሰማኒያ ከመቶ የሚሆኑትና በአንድ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙት ባለይዞታዎች የመሬት ክፍፍል እንዲካሄድ በጽሁፍ ወስነው ጥያቄውን ለባለሥልጣኑ ካቀረቡ ይህንኑ ውሳኔ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ጥያቄው በቀረበበት የይዞታ ሽፋን የመሬት ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል። ተፈፃሚነቱም ውሣኔውን ባሣለፉት ባለይዞታዎች ላይ ብቻ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው የመሬት ሽግሽግ ወይም ክፍፍል ክልከላ በመስኖ የሚለማ መሬትን ለተለያዩ ተጠቃሚዎች የማከፋፈልን ተግባር የሚከለክል አይሆንም።

4. በሕዝብ ጥያቄ መሠረት የመሬት ሽግሽግ ወይም ክፍፍል በሚካሄድበት ጊዜ መሬት ተቀንሶ የሚወሰድበት ባለይዞታ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል እስካልሆነ ድረስ የመረጠውን የመሬቱን ክፍል የማስቀረትና በመሬቱ ላይ ላለማው አንስቶ ሊወስደው ለማይችል ንብረትና መሬቱ ከሚሰጠው ሰው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

9. የመሬት አሰጣጥ ሥርዓትና የሚሰጠው መሬት ዝቅተኛ መጠን

1. የመሬት አሰጣጥ ሥርዓት እንደጠያቂዎች የመሬት ፍላጐት በሕዝብ ተሳትፎ በሚወሰነው ቅደም ተከተል መሠረት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት ላላቸው አመልካቾች ሁሉ ያለአድልዎ እንዲፈፀም ይደረጋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሊሰጥ የሚችለው የመሬት መጠን እኩል የመሬት

2. Notwithstanding the provision of sub-Article 1 of this article, where the land holders residing in one kebele and where not less than 80 Per cent of them request the Authority in writing for land distribution, the land re-distribution may be carried out in accordance with a directive to be issued to implement this decision on the land where question was submitted. Its application shall be only on holders who passed the decision.

3. The prohibition of land re-distribution or allotment provided under sub-article 1 of this Article shall not affect the activities of distribution of irrigable land to various users.

4. When the land distribution or allotment is carried out based on request of people, the land holder whose land is to be decreased and taken shall, where it doesn't bring land division into pieces, have a right to get the land he has chosen and get compensation for an asset he produced and coud not pick it up. The detail shall be determined by a regulation.

9. The Procedure of Land Provision and Minimum Area of Land to be Provided

1. The provision of land shall be made to all applicants, impartially, having a right to acquire land in holding based on petitioners interest and a sequence to be determined by the participation of people.

2. Notwithstanding provision of sub-article 1 of this article, where the land to be distributed is not available to all

ችግር ላለባቸው ጠያቂዎች የማይዳረስ ከሆነ እንደ ቅደም ተከተላቸው ለወላጅ አልባ ሕፃናት፣ ለአቅመ ደካሞች ለሴቶችና ለአዲስ ጎጆ ወጭዎች ቅድሚያ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

3. የሚሰጠው መሬት መጠን በሚወሰንበት ጊዜ የመሬቱ ለምነት ደረጃና ሌሎች በመመሪያ የሚዘረዘሩ ታሳቢዎች ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

4. ለአንድ ሰው የሚሰጠው በዝናብ ወይም በመስኖ የሚለማ የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠን ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

10. <u>የይዞታ ዓይነቶች</u>

በክልሉ የሚገኝ የገጠር መሬት በግል፣ በጋራ፣ በወል ወይም በመንግሥት ሊያዝ ይችላል፡፡

11. <u>ስለይዞታና የመጠቀም መብቶች መከበር</u>

1. የማንኛውም ሰው ይዞታ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም አንቀጽ 28 እንደተደነገገው በሕዝብ ውሳኔ መሠረት በሚደረግ ሽግሽግ ወይም መሬቱን ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው የያዘውን መሬት ከፈቃዱ ውጭ አይነጠቅም፡፡

2. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ከተደነገገው ውጭ የመጠቀም መብቱን አያጣም፡፡

petitioners with equal magnitude of land holding problem it shall priory be caused to be given to orphan children, disables, women and youngsters who join the new life of independence, consecutively.

3. During the time of deciding the area of land to be distributed, the fertility of land and grade, and other assumptions to be stated in the directive shall be considered.

4. The minimum area of plot of land, to be provided to one person and cultivable by rain or irrigation shall, be determined by a regulation to be issued following this Proclamation.

10. <u>Types of Holdings</u>

The land in the region may be held by individually, grouplly, communally, and the government.

11. <u>Respection of Holding and Using Rights</u>

1. The holding of any person is respected by law. Therefore, pursuant to provision of sub-article 2 of article 8 or article 28 of this proclamation, no person shall be expropriated from his holding with out his consent, unless it is done by re-distribution according to decision of people or for the purpose of public interest.

2. Any person provided with a right to use the rural land shall not be deprived from the right to use the land other than provisions of this proclamation or a regulation to be issued to execute this proclamation.

12. የይዞታ መብት የሚታጣባቸው ሁኔታዎች

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ማንኛውም ባለይዞታ በሚከተሉት ምክንያቶች በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ ሊወሰን ይችላል፦

ሀ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ከግብርና ውጭ በሆነ ስራ ላይ የተሰማራና ገቢ የሚያገኝበት ቋሚ መተዳደሪያ ያለው ከሆነ፤

ለ. ያለበት ቦታ ሳይታወቅና መሬቱን ሳያከራይ ወይም የሚያስተዳድርለት ሰው ሳይመድብ በተከታታይ ከ 5 ዓመታት በላይ ከመኖሪያ ቦታው የጠፋ እንደሆነ፤

ሐ. ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ከሶስት ዓመታት በላይ ወይም በመሰኖ የሚለማ መሬት ሲሆን ከአንድ አመት በላይ መሬቱን በጥቅም ላይ ያላዋለ እንደሆነ፣

መ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ የይዞታ መሬቱን በእንክብካቤ ባለመያዙ ምክንያት በመሬቱ ላይ ከባድ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፤

ሠ. የመሬት ይዞታ መብቱን በራሱ ፈቃድ መተውን ለሚመለከተው አካል ያሳወቀ እንደሆነ።

2. የጠፋው ባለይዞታ የትዳር ጓደኛ ወይም አካለመጠን ያልደረሰና አብሮ የሚኖር መሬት የሌለው ልጅ ካለው ወይም የጠፋው ባልተጠበቀ ድንገተኛ ሁኔታ ለመሆኑ የሚያጠራጥር መረጃ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር "ለናሐ" ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም።

12. Conditions Depriving the Holding Right

1. Notwithstanding provision under sub-article 1 of article 11 of this proclamation any holder having a right over using the land, it may be decided to be deprived from the right of using the land by the following reasons:

a) The detail to be determined in regulation, where he is engaged in non-farming activity and earns for his livelihood thereto;

b) Where he disappears from his residence for 5 consecutive years without notifying his where about and not renting his land or without assigning a representative to administer his land;

c) Where he fallows his land for consecutive 3 years and above or 1 year and above where the land is cultivable in irrigation;

d) The detail to be determined by a regulation, where gross damage occurs over his land due to his mismanagement;

e) Where he notifies to the concerned body that he has withdrawn from his holding right.

2. Where a disappeared landholder has spouse or a minor who lives with him and has no land, or where there is a doubtful information that his disappearance is due to unexpected accidental situation., the provision stated under sub Article 1 (b and c) of this Article shall not be applicable.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ለናሐ ድንጋጌዎች መሠረት ባለይዞታው ለጊዜው የጠፋ ወይም አስተዳዳሪ ያልተመደበለት ማናቸውም የገጠር መሬት እንደሁኔታው በተከታታይ ለ3 ዓመት ወይም ለአንድ ዓመት ያህል ጥቅም ላይ አለመዋሉ የተረጋገጠ እንደሆነ መሬት ለሌላቸው ወይም አነስተኛ መሬት ላላቸው አመልካቾች በጊዜያዊነት ጥቅም ላይ እንዲውል ሊሰጥ ይችላል። ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የይዞታ መብቱን ያጣ ማንኛውም ሰው በመሬቱ ላይ ላለማው ቋሚ ንብረት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው መሠረት ተገቢውን ካሣ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

13. ስለመሬት አጠቃቀም

1. ማናቸውም የገጠር መሬት አቅም በፈቀደ መጠን በጥናት የተደገፈ የአጠቃቀም እቅድ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል በኩል ይወጣለታል።

2. የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ የውሃ ተፋሰስን መሰረት አድርጉ የመሬት አጠቃቀምን፣ የአፈር አይነትን፣ የአየር ጠባይን፣ የእፅዋት ሽፋንንና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መዘጋጀት አለበት።

3. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ በሚወጣው የመሬት አጠቃቀም እቅድ መሠረት እንዲገለገል ይደረጋል።

4. ማንኛውም መሬት ለአንድ አገልግሎት እንዲውል ሲደረግ :-

   ሀ. የተሻለ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚሰጥ መሆኑ፣

   ለ. በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ አለመኖሩ ወይም ተጽእኖው አነስተኛ መሆኑ፣

3. Pursuant to provisions of sub-article 1(b and c) of this Article, where the land holder disappears or the land administrator is not assigned, ascertaining that it was fallow for 3 consecutive years, may temporarilly be given to those who do not have land or have small land holding up on their petition. The detailed execution shall be determined by a regulation.

4. Any person who is deprived from his land holding right pursuant to sub-article 1 of this article, shall have a right to get compensation for the permanent property he had developed on the land in accordance with the regulation to be issued to implement this proclamation.

13. Land Use

1. Any rural land shall, as much as possible, have land use plan issued by the concerned body based on study.

2. The rural land use plan shall be prepared considering land usage, soil type, air condition, vegitation coverage, and socio-economic situations based on water catchments.

3. Any land user shall be made use in accordance with land use plan to be issued thereof.

4. Where any land is made for a given service:

   a) Its better economic benefit provision,

   b) The non-or least existence of side effects on the environment,

ሐ. አገልግሎቱ በተጠቃሚዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑ እየተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. አግባብ ካለው አካል በጽሁፍ ተዘጋጅቶ የተሰጠ የመሬት አጠቃቀም እቅድ የሌለ እንደሆነ ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ መሬቱን ለቤት መሥሪያ፣ ለእርሻ፣ ለእንስሳት እርባታ፣ ለደን ልማት ወይም ከእነዚሁ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሌሎች ተግባራት ሊገለገልበት ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ተጠቃሚ መሬቱን በሕግ ለተከለከለ ተግባር ሊያውለው አይችልም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

14. ስለመስኖ መሬት

1. በዘመናዊ መስኖ የሚለማ ማናቸውም መሬት የቀድሞ ባለይዞታ የሚገባውን ድርሻ በቅድሚያ እንዲያገኝ እየተደረገ እንዲሸጋሸግ ሊደረግ ይችላል፡፡

2. የመስኖ መሬቱ በሽግሽግ የተወሰደበት አርሶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አደር በተቀነሰው መሬት ላይ ላለማው ቋሚ ንብረት መሬቱ በሚሰጠው ሰው በኩል የሚተካ ካሣ በቅድሚያ ይከፈለዋል፡፡

3. ባህላዊ የመስኖ አጠቃቀም በአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ ደንብና በሚመለከታቸው የሙያ መ/ቤቶች ምክር ተደግፎ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

4. የሚመለከታቸው የሙያ መ/ቤቶች የሚያወጧቸውን መመዘኛዎች ተፈፃሚ የማድረጉ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ዘመናዊ የመስኖ ልማት ሥራ ከመካሄዱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ጥናቶች መደረጋቸውን፣ ለሚገነባው ግድብ አስፈላጊው የተፋሰስ ሥራ መከናወኑንና በግድቡ ግንባታ ምክንያት ተቆፍሮ የሚወጣው አፈርና ድንጋይ በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

c) The acceptability of the service by beneficiaries shall be ascertained.

5. Where there is no land use plan prepared in writing by pertinent body, any land user may use his land for house construction, farming, animal husbandary, forestry development, or for other related same activities.

6. Notwithstanding the provision stated under sub-article 5 of this article, any land user cannot use his land for legally prohibited activity. The detail shall be determined by a regulation.

14. Irrigation Land

1. Any land to be cultivated by modern irrigation may, causing the acquisition of proper share of the previous landholder, be distributed.

2. Farmer or semi-pastoralist whose land is taken by distribution shall, priory be paid compensation through the person to whom his land is to be given for permanent assets he cultivated on decreased land.

3. The traditional irrigation usage shall be carried out supported by community cultural rules and counseling of the pertinent professional offices.

4. Without prejudice to the obligations to apply the requierements to be issued by professional offices, before any modern irrigation activity is carried out, it shall be necessary to ensure the undertaking of the detailed design works for the dam to be constructed, conducting of the catchment works, and the non-damaging of the soil and stone dug during the dam construction on public.

5. የመስኖ ልማት ሲካሄድ ለአካባቢው ህብረተሰብ የበሽታ ምንጭ እንዳይሆንና የአፈር መሸርሸርን እንዳያስከትል ተጠቃሚዎች ይህንኑ የመከላከል ግዴታ አለባቸው፡፡

6. በመሬታቸው ላይ የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታና የውሃ ግድብ የተሰራባቸው ባለይዞታዎች በመስኖ ከሚለማው መሬት ውስጥ ትክ ቦታና በመሬቱ ላይ ላለሙት ንብረት በግድቡ ተጠቃሚዎች የሚተካ ተገቢው ካሣ በቅድሚያ ይከፈላቸዋል፡፡

7. በመስኖ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ለመስኖ መሠረተ ልማት አውታሮችና ለተፋሰሱ ከመንግሥት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ጥንቃቄና ጥበቃ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

ክፍል ሦስት

የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብቶችን ስለማስተላለፍና ስለግዴታዎች

15. የመሬት ይዞታ መብትን ስለማስተላለፍ

1. የገጠር መሬት ይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን ከዚህ በታች በተደነገገው አኳኋን በውርስ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሠፈረው መብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት መሬት በይዞታ ለተሰጣቸው ድርጅቶች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

5. The beneficearies shall be duty bound to control their area not to be source of disease and not to cause erosion while irrigation development takes place.

6. The land holders, on whose land the irrigation infrastructure and water dam are built, shall be provided with irrigable land substitution, and be paid compensation priorly which it may be substituted by the would be dam users for their assets cultivated on their land.

7. The society using irrigation shall be duty bound to take care and guard of the irrigation infrastructure and catchment in collaboration with the government.

PART THREE

Transfer and Obligations of Land Holding and Use Rights

15. Transfer of Land Holding Right

1. Any person provided with rural land holding may, as stipulated herein under, transfer his holding right in bequeath or donation .

2. Without prejudice to provision of sub-Article 4 of Article 17, here of, the right stated under sub-article 1 of this Article shall not be applicable on organizations that are provided with holding land pursuant to sub article 4 of Article 6 of this Proclamation.

16. የመሬት ይዞታ መብትን በውርስ ስለማስተላለፍ

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ መተዳደር ለሚፈልግ ማንኛውም አርሶ አደር በኑዛዜ ማስተላለፍ ይችላል።

2. ለውርስ ዓላማ ሲባል የገጠር ኑሮአቸውን ለመደጎም ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ እየሠሩ በከተማ የሚቀመጡ ሰዎች እንደ አርሶ አደር ይቆጠራሉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው የይዞታና የመጠቀም መብትን በኑዛዜ የማስተላለፍ ወይም የማውረስ መብት አካለመጠን ያላደረሰውን የተናዛዡን ልጅ ወይም ቤተሰብ ከወራሽነት መብት ከህግ ውጭየሚነቅል ወይም የተናዛዡን የትዳር ጓደኛ የሚጎዳ ሆኖ ከተገኘ በሕግ ፊት የሚፀና አይሆንም። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

4. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የይዞታና ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብቱን በኑዛዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

5. አንድ የመሬት ባለይዞታ የይዞታና የመጠቀም መብቱን በተመለከተ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ መብቱ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ መተዳደር ለሚፈልግ የሚቹ ልጅ ወይም ቤተሰብ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት ይተላለፋል።

6. አንድ ሰው ሳይናዘዝ በሞተበት ወቅት በክልሉ ውስጥ የሚኖርና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ ልጅ፣ ወይም ቤተሰብ የሌለው እንደሆነ ወላጆቹ በክልሉ ውስጥ ነዋሪዎች ሆነው በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የሚፈልጉ ከሆኑና አስቀድሞ ያላቸው

16. Transfer of Land holding right in Bequeath

1. Any Person who is made the holder of the rural land in accordance with this proclamation, may transfer his holding or using right in will to any farmer engaged or likes to engage in agricultural works.

2. Persons residing in town and engaged in small income activities to support their lives shall be considered farmer for the aim of succession.

3. Transferring in will or inheriting the holding and use right, stipulated under sub-article 1 of this Article, shall not be valid where it disinherites the minor child of the testater or the family of same from inheritance right or harms his spouse. The detail shall be determinded by a regulation.

4. Any land holder may, in will, transfer his holding and for limited period of time his use right to more than one persons.

5. Where a land holder dies without making a will, as to the holding and use right of his land, the right shall be transferred to his child or family engaged or likes to be engaged in agricultural works, consecutively, in accordance with the provisions of a regulation to be issued to implement this proclamation.

6. Where a man dies without making a will and he does not have a child residing in the region and engaged or like to be engaged in agricultural works, or where he does not have family, his parents who are residents of the region engaged or like to be engaged in agricultural

የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ከከፍተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆኑ ከታወቀ የመሬት ይዞታውን የመውረስ መብት ይኖራቸዋል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው የወራሾች መብት በሕይወት ያለው የትዳር ጓደኛ በዚያው ቀበሌ ውስጥ መኖሩን ከቀጠለ ሌላ ጋብቻ እስኪፈጽምና ካላገባ ደግሞ በህይወት ዘመኑ በመሬቱ ላይ እየተጠቀመ ከመቆየት የሚከለክለው አይሆንም። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

8. ከአንድ በላይ የሆኑ ወራሾች በውርስ ያገኙትን መሬት በሚከፋፈሉበት ጊዜ የእያንዳንዳቸው ድርሻ በደንቡ ከተወሰነው የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠን በታች የሆነ እንደሆን መሬቱን በጋራ መጠቀም እንጂ መከፋፈል አይችሉም።

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 5 ወይም 6 ድንጋጌዎች መሠረት ወራሽ ያልተገኘለት የገጠር መሬት በባዶ ቦታነት ተመዝግቦ ለአዲስ አመልካቾች ይከፋፈላል።

17. የይዞታና የመጠቀም መብትን በስጦታ ስለማስተላለፍ

1. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በክልሉ ውስጥ ለሚኖርና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ ይችላል፦

works and priory known for holding the land less than the maximum holding area, shall have a right to inherit the land holding.

7. The right of heirs provided under sub-Article 6 of this Article shall not have prohibition to stay using the land where the alive spouse continues to reside in that kebele until he concludes another marriage and where he does not do so it remains for his lifetime. Particulars shall be determined by a regulation.

8. Where more than one heirs share the inherited land, and where the share of each heir is less than the minimum plot of land holding determined by a regulation, they shall not partition the land other than using it in common.

9. The rural land that does not gain heir pursuant to the provisions of sub-Article 1, 5 or 6 of this Article, shall, registred as vacant land, be distributed to the new petitioners.

17. Transfer of Holding and using Right in Donation

1. Any land holder may transfer his holding or using right in donation to a person who resides in the region and fulfills the preconditions indicated here in under:

ሀ. ተቀባዩ በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ የክልሉ ነዋሪ ሆኖ ምንም አይነት መሬት የሌለው ወይም አስቀድሞ በያዘው መሬት አነስተኛነት ምክንያት ሌላ መሬት እየተከራየ የሚያርስ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ወይም ሌላ የቤተሰቡ አባል ከሆነ፤

a) Where the donee is child or grand child or other family member engaged or likes to be engaged in agricultural works, being the resident of the region, and not holding any land, or tills land by renting from others due to his previous small holding.

ለ. ተቀባዩ የባለይዞታውን መሬት እያረሰ ወይም ሌላ ስራ እየሠራ ስጦታው ከመከናወኑ በፊት ላሉት 3 ተከታታይ አመታት ሰጭውን በነፃ ሲጦር መቆየቱ የታወቀ ከሆነ::

b) Where the donee had stayed tilling the land of the holder or working other works and known freely cared for 3 consecutive years before the gift is undertaken.

2. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በቋሚነትና የመጠቀም መብቱን ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ለተለያዩ ሰዎች በስጦታ ሊያስተላልፍ ይችላል::

2. Any landholder may transfer permanently his holding right and temporarily his using right to deferent persons in gift.

3. የመሬት ይዞታው የባልና ሚስት የጋራ ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ በሚሆንበት ጊዜ ስጦታው የሚፀናው ባልና ሚስቱ ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች ሁሉም ከተስማሙ ብቻ ይሆናል::

3. Where the land holding is a common holding of a husband and wife or other persons, the gift shall only be applicable in agreement of all the husband and wife or other common holders.

4. የይዞታ መብታቸውን ሣይጨምር ድርጅቶች በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ለተወሰነ ጊዜ በስጦታ ማስተላለፍ ይችላሉ::

4. Organizations may, excluding holding right, transfer their land using right for limited period of time in donation.

5. ማናቸውም የስጦታ ስምምነት በጽሁፍ መደረግ አለበት:: በቃል የተደረገ የስጦታ ስምምነት በሕግ ተቀባይነት አይኖረውም::

5. Any gift agreement shall be in writing. An agreement made orally shall not be acceptable by law.

6. በፅሁፍ የተደረገ ማናቸውም የስጦታ ስምምነት መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ አለበት::

6. Any gift agreement made in writing shall be submitted to and registered in the woreda branch office of the Authority.

18. በመሬት የመጠቀም መብትን በኪራይ ስለማስተላለፍ

1. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን ለማንኛውም ሰው በኪራይ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2. ከሦስት ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ የተደረገ ማናቸውም የመሬት ኪራይ ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት፡፡

3. በጽሁፍ የተደረገ የመሬት ኪራይ ስምምነት የመሬቱን ስፋት፣ የኪራዩን ዘመን፣ የክፍያውን መጠንና የኪራዩን አከፋፈል ሁኔታ የሚገልጽ ካልሆነ በስተቀር ፈራሽ ይሆናል፡፡

4. የሚከራየው መሬት በጋራ የተያዘ ከሆነ ሁሉም ባለይዞታዎች ካልተስማሙበት በስተቀር ውሉ ፈራሽ ይሆናል፡፡

5. በፅሁፍ የተደረገ ማናቸውም የመሬት ኪራይ ስምምነት መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

6. ከፍተኛው የመሬት ኪራይ ዘመን 25 ዓመት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከ25 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ተደርጐ የተገኘ የመሬት ኪራይ ስምምነት ቢኖር በዚህ አዋጅ መሠረት ለ25 ዓመት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው የኪራይ ዘመን ጣሪያ የውሉ ዘመን ሲያበቃ እንደገና ሊታደስ የሚችልበትን እድል የሚከለክል አይሆንም፡፡

18. Transferring Land Use Right in Rent

1. Any land holder may transfer his using right in rent to any person.

2. Any land rent agreement made for more than 3 years shall be made in writing.

3. Any land rent agreement made in writing unless it explains area of the land, year of the rent, the amount and system of payment, shall be invalid.

4. Where the land to be rented is a common holding, the agreement shall be invalid, unless all holders agree upon it.

5. Any land rent agreement made in writing shall be submitted to and registered in the branch office of the Authority, in woreda where the land is found.

6. The maximum duration of rent time may be 25 years. Therefore, any agreement made for more than 25 years shall be considered as only made for 25 years land rent agreement pursuant to this proclamation.

7. The period of the limit of rent provided in sub-Article 6 of this Article shall not ban its renewability after the completion of the agreement period.

8. ከግል ባለይዞታዎች ጋር በሚደረግ የመሬት ኪራይ ስምምነት የሚከፈለው የኪራይ መጠን አከራይና ተከራዩ በሚያደርጉት ድርድር የሚወሰን ይሆናል::

9. በኪራይ ስምምነቱ ውስጥ እንደገና የማከራየት መብት ያለው መሆኑ በግለጽ ካልተመለከተ በስተቀር ተከራዩ መሬቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለ3ኛ ወገን ሊያከራየው አይችልም::

19. በሊዝ ስርዓት የተገኘ በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን የዕዳ ዋስትና አድርጐ ስለማስያዝ

1. የገጠርን መሬት በሊዝ የተከራየ ማንኛውም ባለሃብት የሊዝ ዘመኑ ፀንቶ ለሚቆይበት ጊዜ በተከራየው መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ወይም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሃብት ወይም ሁለቱንም በዕዳ ዋስትናነት ለማስያዝ ይችላል::

2. ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመሬት የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትናነት ከተያዘ በመሬቱ ላይ የለማው ሀብትም አብሮ እንደተያዘ ይቆጠራል:: ሆኖም በመሬቱ ላይ የለማው ሀብት ተነጥሎ በዕዳ ዋስትናነት የሚያዝ ቢሆን በመሬት የመጠቀም መብቱ አብሮ እንደተያዘ አያስቆጥረውም::

3. የዕዳ ዋስትና ሆኖ የተያዘን በመሬት የመጠቀም መብት ባለገንዘቡ አስቀድሞ ካልተስማማ በስተቀር የአበዳሪውን ጥቅም በሙሉ ወይም በከፊል በሚጎዳ ሁኔታ በኪራይ ማስተላለፍ ፣ በሌላ መሬት መለወጥ ወይም በሌላ ሁኔታ የይዞታ ለውጥ ማድረግ አይቻልም::

8. The amount of rent to be paid in agreement with private holders may be determined by agreement to be made between the lessor and the lessee.

9. Unless it is clearly indicated in the rent agreement that the lessee has right to re-rent, he shall, partially or fully, not rent the land to the third party.

19. Mortgage of Rural Land Use Right Obtained in Lease System

1. Any investor who rented rural land in lease may secure as mortgage right to use his land or an asset produced on it, or both for effected period of the lease.

2. Unless there is a contrary agreemet, where the land use right is mortgage pursuant to sub-Article 1 of this Article, the asset developed on the land shall be considered as it is with held together. However, where only an asset produced on land is mortgage, the land use right shall not be considered as mortgage together with same.

3. Unless the creditor priory agrees, it may not be possible to transfer the right to use the land obtained by mortgage in rent, change by another land or change the holding in any other situation that may harm the creditor fully or partially.

4. በመሬት የመጠቀም መብትን በእዳ ዋስትናነት የማስያዝ ስምምነት በጽሁፍ መደረግ አለበት፡፡ የስምምነቱ መግለጫ ጽሁፍም መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡

5. በዚህ አዋጅ መሰረት በመሬት የመጠቀም መብት ወይም በመሬቱ ላይ የለማ ሃብት በእዳ ዋስትናነት ሊያዝ የሚችልበት ጊዜ ከ25 ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

20. የመሬት ተጠቃሚ ግዴታዎች

1. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

   ሀ. በይዞታው ስር ያለውን ወይም በኪራይ የተሰጠውን መሬት የመንከባከብና አካባቢውን የመጠበቅ፤

   ለ. በመሬቱ አካባቢ ዛፎችን የመትከልና በተገቢው ሁኔታ ተንከባክቦ የማሳደግ፤

   ሐ. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ30 በመቶ በታች የሆኑ መሬቶችን በተመለከተ የአፈር ክለትን የሚቀንስና ውሃ የሚሰበስብ ስልትን የተከተለ የመሬት አያያዝን የመከተል፡፡

   መ. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ31 በመቶ እስከ 60 በመቶ የሆኑ መሬቶችን ለአመታዊ ሰብሎች ልማት ለማዋል ይቻል ዘንድ ጠረጴዛማ እርከን ወይም ሌሎች ተስማሚ የአፈር ጥበቃ ሰራዎችን የማከናወን፤

   ሠ. ተገቢ ባልሆነ አስተራረስ ሣቢያ ምንጮች እንዳይደርቁ ጥንቃቄ የማድረግ፤

4. The agreement of securing land use right in mortgage shall be made in writing. Unless the clarification of the agreement is submitted to and register in branch office of the Authority where the land is found, it shall not affect the right of third parties.

5. In accordance with this proclamation, the right to use land or the duration to mortgage the resource developed on the land shall not exeed 25 years.

20. Obligations of the land user

1. Any land user shall, pursuant to this proclamation, have obligations indicated hereinunder:

   a) To protect the land under his holding or land obtained in rent and conserve the surrounding;

   b) To plant trees around his land and properly protect them to grow;

   c) To follow the land holding system that decreases soil erosion and collect water concerning the lands under 30 per cent slope;

   d) To undertake trench terracing and favorable soil conservation activities to use the land forms which are 31 to 60 per cent slope for perennial plants.

   e) To take care of water sources not to go dry due to improper farming;

ረ. ወሰናቸው የተከለለ መሬቶችን ድንበር ያለመጋፋትና ተለይተው የሚታወቁ መንገዶችን ያለመዝጋት፤

ሰ. መሬቱን በመሬት አጠቃቀም እቅድ መሠረት እንዲጠቀም አግባብ ባለው አካል በጽሁፍ ሲጠየቅ ተግባራዊ የማድረግ፤

ሸ. በመሬቱ አካባቢ የሚገኙ የዱር እንሰሳትና አእዋፍ እንዳይጎዱ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ፤

ቀ. መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ሥራ እንዲካሄድበት አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለዚሁ የመተባበር፤

በ. የመሬቱ ባለይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በሚሰጥበት ጊዜ ይህንኑ የማውጣትና የመያዝ፤

ተ. የመሬት ይዞታ መብቱን በሚያጣበት ጊዜ የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አግባብ ላለው አካል የመመለስ::

2. መሬቱ በወንዝ ዳር ወይም በገደል አካባቢ የሚገኝ ማንኛውም ተጠቃሚ ከወንዙ ወይም ከገደሉ አርቆ የማረስ ግዴታ አለበት::

3. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ የሆነ የግል ባለሃብት ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገጉት ግዴታዎች በተጨማሪ ለተፈቀደለት መሬት የአጠቃቀም ፕላን አቅርቦ የማስፀደቅና በተፈቀደው ፕላን መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ አለበት:: የሚቀርበው የአጠቃቀም ፕላንም የህብረተሰቡን ጤንነት፣ የአካባቢውን ደህንነትና የመሬቱን ለምነት መጠበቅ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል::

f) Not to violate delineations of lands and close roads thereto.

g) To use land based on land use plan when asked by pertinent body in writing to use it same;

h) To exercise proper care for wild lives and birds found around his holding;

i) To cooperate with pertinent body when asked for measuring or undertaking surveying on his land;

j) To take and hold a certificate where he is a land holder and land holding certificate is issued;

k) To return back to the pertinent body. The land holding certificate, when he is deprived of holding.

2. Any land user shall have an obligation to plough his land far from river or gully where his land is near to a bank of a river or gully.

3. Any Private investor or organization, besides obligations provided under sub-Article 1 of this Article, shall sumbit and cause approval of land use plan, and use the land in accordance with the approved plan. The plan to be submitted shall consider the health of the society, the security of the surrounding and the fertilty of land.

4. መሬትን በመንከባከብና አካባቢን በመጠበቅ ረገድ አርአያነት ያለው ሥራ ለሚያከናውኑ የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች ባለሥልጣኑ አቅሙ በፈቀደ መጠን የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል።

21. ግዴታን አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ኃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 የተደነገገውን የትኛውንም ግዴታ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ የተደነገገውን ተመሳሳይ ግዴታ ያላከበረ የመሬት ባለይዞታ የቃልና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በቅደም ተከተል ይሰጠዋል።

2. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ስህተቱን ሊያርም ያልቻለ እንደሆነ ከዚህ በታች በተደነገገው መሠረት አስተዳደራዊ ርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡-

   ሀ. በራሱ ድክመት መሬቱን ባለመንከባከቡ ምክንያት በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመጠቀም መብቱን መሬቱን ለመንከባከብ ግዴታ ለሚገባ ሌላ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ እንዲሰጥ የሚተላለፍ ውሣኔ፤

   ለ. ከዚህ በላይ የተመለከተው እርምጃ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ በመሬት የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ካሣ ተከፍሎት መሬቱን እንዲለቅ እስከመገደድ የሚደርስ እርምጃ።

3. ማንኛውም የወል መሬት ተጠቃሚ መሬቱን ለመንከባከብ ከሕብረተሰቡ ጋር አልተባበርም ካለ ሀግ ባለማክበሩ ምክንያት እንደቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም እንዲደርሰው ይደረጋል።

4. The authority shall, as much as its extent, give motivating prize for the land holders and users who perform exemplary activities in land conservation and environmental protection.

21. Effects of Non-Performance of Obligation

1. Any land holder who failed to respect any obligation provided under Article 20 of this Proclamation or similar provisions of a regulation to be issued to execute this Proclamation, shall be given oral and written notice respectively.

2. Where the land holder could not correct his mistakes in accordance with the notice, administrative measures may be taken as provided herein under:

   a) Where his land is degraded due to his weakness, not to conserve it, by a decision to be passed to transfer his right to use land in rent temporarily for a person who undertaks an obligation ;

   b) Where the offense is committed again after the measure indicated herein above is executed, a measure from suspending him from using right for a limited time up to expropriating from his land paying him compensation.

3. Where any communal land user refuses to cooperate with the society to conserve land, he shall,respectively, be given oral or written notice for his refusal.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ የወል መሬቱን እንዳይጠቀምበት ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ለዘለቄታው በወል መሬቱ እንዳይጠቀምበት እስከመከልከል የሚደርስ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል።

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 የተደነገጉትን ሌሎች ግዴታዎች ያላከበረ የመሬት ተጠቃሚ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ሥር ከተመለከቱት ርምጃዎች በተጨማሪ ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ካሣ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይችላል።

6. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ የተደነገጉት ኃላፊነቶች ግዴታቸውን ባልተወጡ የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በሆኑ መንግሥታዊ መ/ቤቶች ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የብዙሃን ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት ላይም እንዳግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ክፍል አራት
መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና ስለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

22. መሬትን ስለመለካት

1. ለተጠቃሚዎች በይዞታነት የተሰጠ፣ በአንድ አካባቢ ማህበረሰብ አማካኝነት በወል መጠቀሚያነት የተያዘ ወይም ለደን ልማት ወይም ለሌሎች መሠል ተግባራት የተከለለ የትኛውም የገጠር መሬት በባህላዊ መንገድ ወይም በዘመናዊ መሣሪያ በባለሥልጣኑ አማካኝነት ተለክቶ ካርታ ይዘጋጅለታል። በዚህም ሣቢያ እያንዳንዱን መሬት በግልጽ ለመረዳት የሚያስችል የመሬት ልዩ ቁጥር አሰጣጥ ሥርዓት ተቀርጾ በስራ ላይ ይውላል። የመሬቱን ድንበር የሚያሳይ ምልክትም በመሬቱ ላይ ይደረጋል።

4. Where the offense committed is similarly repeated after the notice provided under sub-Article 3 of this Article, he may be penalized from suspending to use the land temporarily to banning from using the communal land totally.

5. A land user who did not respect other obligations provided under Article 20 of this Proclamation , shall be made to pay compensation for the damage pursuant to civil code in addition to measures indicated under sub-Article 3 and 4 of this Article.

6. Responsibilities provided in this Article shall, upon failure to carry out obligations, be applicable on rural land holder or user government offices, non-government organizations, civic societies and religious institutions, as it may be appropriate.

PART FOUR
Measuring, Registering and Holding Certificate of Land

22. Measuring Land

1. Any Rural Land given to users in holding, held for common usage by the community of an area, or forestry development, or conserved for any other similar activities shall be measured and the map get prepared by the Authority in traditional way or modern tool. Because of this, a special system of numerating shall be designed and implemented to clearly understand each land. The sign that indicates the boundary shall,also, be made on the land.

2. ማናቸውም መሬት በሚለካበት ጊዜ በተቻለ መጠን የሚለካው መሬት አዋሳኝ ባለይዞታዎች ወይም ተጠቃሚዎች በስፍራው እንዲገኙና ድንበራቸውን በስምምነት እንዲወስኑ ጥሪ ይደረግላቸዋል። የመሬቱ ቅየሳ የሚካሄደውም የባለይዞታዎችን ማሳዎች በመነሻነት በመጠቀም ይሆናል።

3. በመሬቱ አለካክና በድንበሩ አከላለል ረገድ ቅሬታ የተሰማው ባለይዞታ ቅር የተሰኘበትን ምክንያት ገልጾ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ለሚመለከተው አካል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

4. መሬቱ ከተለካ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት መጠኑ ከተለወጠ እንደገና ተለክቶ አዲስ ካርታ ይዘጋጅለታል።

5. ፈቃድ ያላቸው የግል የቅየሳ ድርጅቶች በመሬት ቅየሳ ሥራው እንዲሳተፉ ሊደረግ ይችላል።

23. ስለመሬት ምዝገባና የመረጃ አያያዝ

1. በዚህ አዋጅ መሰረት በባለሥልጣኑ የተለካ ማናቸውም መሬት በገጠር መሬት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረውን ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የመሬት ምዝገባው የመሬቱን ባለይዞታ ሙሉ ስም፣ ይዞታው የተገኘበትን ሁኔታ፣ የመሬቱን አዋሳኞች፣ የለምነቱን ደረጃ፣ መሬቱ የሚውልበትን አገልግሎትና ባለይዞታው ያሉበትን ግዴታዎች የሚገልጽ መረጃ አካቶ መካሄድ ይኖርበታል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. When any land is measured the neighboring land holders or users shall, as much as possible, be called to attend therein and decide upon their boundary in agreement. The survey of the land may be conducted by using the plots of holders as a starting point.

3. The land holder who complains regarding the land measurement and delineation, he may submit petition to the concerned body explaining his reasons of complaint by the time limit to be decided by a regulation to be issued following this proclamation to make the case to be seen again.

4. Where, for different reasons, the area of the land is changed after it has been measured, it shall be measured again and a new map get prepared thereof.

5. Private survey organizations having a license may be made participate in land survey activity.

23. Registration and Data Maintaining

1. Any land measured by the Authority shall, pursuant to this proclamation, registered in rural land registration book.

2. To implement the provision indicated and sub-Article 1 of this Article, the land registration shall be carried out including the information explaining the full name of the land holder, the conditoins of holding acquired, boundaries of the land, the fertility standard, the service of the land and the obligations of the land holder. The detail shall be determined by a regulation.

3. በመሬቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም እንዳላቸው ማስረዳት የሚችሉ ሰዎች ሁሉ አግባብ ላለው አካል ጥያቄ በማቅረብ ሲፈቀድላቸው ይህንኑ መዝገብ ማየት ይችላሉ፡፡

4. ከመሬቱ ጋር የተያያዘ ማናቸውም መብትና ግዴታን የሚመለከት ተግባር መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

5. በሃሰተኛ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የተካሄደ ምዝገባ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

6. የመሬት መመዝገቢያ መዝገብ በሁለት ቅጅ ተሠርቶ ዝርዝራቸው በደንብ በሚወሰነው አካላት እጅ ይቀመጣል፡፡ የመዝገቡ ማጠቃለያ ለባለሥልጣኑ ይላካል፡፡

7. በመዝጋቢው ስህተት ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ስህተቱ የሚመለከተው የመንግሥት አካል በፍትሐብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ምክንያት የሚመለከተው የመንግስት አካል በስህተቱ ለተጐዳው ወገን ካሣ እስከመክፈል የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ እንዲመልስለት ስህተቱን የሠራውን መዝጋቢ ሠራተኛ በተራው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም መዝጋቢው በኃላፊነት የሚጠየቀው ስህተቱን የሠራው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

9. በወረዳዎች የሚገኙ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች የመሬት ምዝገባውን በአግባቡ እንዲያካሂዱ አስፈላጊውን እገዛ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. Those people who can explain that they have a right or interest over the land, may, submitting question to the concerned body, see the book upon permission.

4. Unless any activity concerned with the right and obligations related to land is submitted and registered in woreda branch office of the Authority, it may not be an objection to the third parties.

5. Registration carried out based on false information shall not have legal effect.

6. The land registration book shall be prepared in two copies and kept on the hands of the bodies whose details shall be determined by regulation. The summary of the book shall be sent to the authority.

7. Where a damage occurs on any person due to the fault of the registrar,the body of the government which is attributed with the fault shall be accountable to the civil liability.

8. Where the concerned government body approaches up to paying compensation to the victim due to the fault upon the implementation of provision of sub-Article 7 of this Article, it shall have the right to claim from the registration worker who committed the fault to reimburse the payment.However, the registrar will be liable when he commits the fault intentionally or negligently.

9. The branch offices of the authority in the woredas shall have a responsibility to give the necessary support to the Kebele Land Administration and use committees to properly carry out the land registration.

24. ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

1. የገጠር መሬት በይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ዝርዝር የተመዘገበበት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶና ፎቶግራፉ ተለጥፎበት በባለሥልጣኑ ይሰጠዋል። የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታው በሕግ የተጠበቀ መብት ማስረጃ ነው።

2. መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ይዞታ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ የሚዘጋጀው በሁለቱም ስም ይሆናል።

3. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ይዞታ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ።ባልና ሚስት የግል የነበረውን መሬት በስምምነት የጋራ በሚያደርጉበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ የሚታደሰው ያለምንም ክፍያ በነፃ ይሆናል።

4. ተቃራኒ የጽሁፍ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ የተሰጠው ሰው የመሬቱ ሕጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል።

5. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታውን በሕግ የተደነገጉ ዋና ዋና መብቶችና ግዴታዎች ማመልከት አለበት። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

6. በሕግ ከተወሰነው የአንድ ማሳ ዝቅተኛ መጠን በታች የሆነ መሬት በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ውስጥ ለብቻ አይመዘገብም። ሆኖም የዚህ አይነት መሬቶችን በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተዘጋጅቶ የሚሰጥበት ሁኔታ ወደፊት በደንብ ይወሰናል።

24. Land Holding Certificate

1. Any person, granted rural land shall be given the land holding certificate in which the details of the land is registered by the Authority prepared by his name and his photograph fixed thereon. The holding certification is a legal certificate of the holder.

2. Where the land is a holding of a husband and a wife in common, the holding certificate shall be prepared by the name of both spouses .

3. Where marriage is concluded after the certificate is given in the name of a spouse, they may agree to make the land common holding. Where the spouses make the land that was individual holding to common holding, the holding certificate may be renewed freely, without any payment.

4. The person who is granted the land holding certificate in his name shall, unless a contradictory written document is submitted, be considered legal holder of the land.

5. The land holding certificate shall indicate the main provisions of right and obligations of the land holder. The detail shall be determined by a regulation.

6. The land which is less than the minimum limit of holding shall not be registered alone in the book of land holding certificate. However, concerning such lands the preparation and provision of land holding certificate shall be determined by a regulation in the future.

7. ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈላጊውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሳያወጣ በገጠር መሬት ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ባለይዞታ ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ መሬቱን እስከማስለቀቅ ለመድረስ የሚችል ርምጃ ይወሰድበታል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

ክፍል አምስት
ኃላፊነት ስላለባቸው አካላት

25. ስለልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት

1. ባለሥልጣኑ አግባብ ያላቸውን አካላት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህንን አዋጅ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የግል ተቋማት ከመሬት አጠቃቀም ወይም አጠባበቅ ጋር ግንኙነት ያለውን ማናቸውንም ሥራ በሚያከናውኑበት ወይም መሬትን ለተለያዩ ተግባራት በሚጠቀሙበት ጊዜ በዚህ አዋጅ የሰፈሩትን ግዴታዎች የመፈፀም ኃላፊነት አለባቸው።

3. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤቶች ድንበራቸው በግልጽ እንዲካለል በማድረግ የአዋጁን ተፈፃሚነት የመደገፍ ኃላፊነት አለባቸው።

26. ስለባለሥልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊነት

በወረዳ ደረጃ የተቋቋመ የባለሥልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት ይህንን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. በባለሥልጠኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 47/1992 ዓ.ም. አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4

7. Where any person is found using rural land without taking the necessary rural land holding certificate without sufficient and legal reason, a measure starting from notice to displacing from land shall be taken. The detail shall be determined by a regulation.

PART FIVE
The Responsible Bodies

25. Responsibility of Various Offices

1. The Authority shall have responsibility to implement this proclamation by coordinating the pertinent bodies and providing professional support.

2. Government offices and private institutions found in the region shall have responsibility to implement obligations stated in this proclamation when they carry out any activity that has a relation to land use or conservation or when they use the land for different activities.

3. The Woreda and Kebele Administration Councils shall have responsibility to support the implementation of the proclamation causing the clear delineation of their boundaries.

26. The Responsibility of the Woreda Accountable Office of the Authority.

The accountable Office of the Authority established at Woreda level, shall have the following duty and responsibilities in regard to implementing this proclamation.

1. Establishes land Administration and use committees through public election in Kebeles and sub-kebeles pursuant to

ድንጋጌ መሠረት በቀበሌዎችና በንዑስ ቀበሌዎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችን በሕዝብ ምርጫ ያቋቁማል። ሴቶች በነዚሁ ኮሚቴዎች አባልነት በተቻለ መጠን ከወንዶች ጋር በተመጣጠነ ቁጥር መመረጣቸውን ያረጋግጣል፤

2. በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የተቋቋሙ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችን ይከታተላል፣ የመሬት አስተዳደሩ ተግባር አዋጁ በሚጠይቀው መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ለተመረጡ የኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነታቸውን አስመልክቶ ተገቢውን ሥልጠና ይሰጣል፤

4. የመሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል።

27. ስለቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ

1. በቀበሌ ደረጃ የተቋቋመ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በቀበሌው ውስጥ ባለሥልጣኑ ከሚሰይመው ወይም ከሚመድበው ባለሙያ ጋር በመተባበር ይህንን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ. በቀበሌው ውስጥ የሚገኘውን መሬት ያስተዳድራል፣ የመሬት አጠቃቀም በህዝብ ተሳትፎና በወረዳው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ትብብር እንዲወሰን ያደርጋል።

ለ. የሚቀርብለትን የመሬት ጥያቄ ተቀብሎ በሕዝብ ተሳትፎ እየታገዘ ቅደም ተከተል በማስያዝ እደላው የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

provision of sub-Article 4 of Article 8 of the proclamation No.47/2000 that establishes the Authority. It ensures the election of women to these committees membership be balanced to that of men.

2. Follows the land Administration and Use Committees established at kebele and sub-kebele level; controls the undertaking of the activity of the Land Administration is being implemented as per the Proclamation.

3. Gives appropriate training to the committee members elected pursuant to the provision of sub-Article 1 of this Article concerning their duty and responsibilities.

4. Properly handles and keeps data concerning the land administration and use.

27. Kebele Land Administration and Use Committee

1. The Land Administration and Use Committee established at kebele level shall, in cooperation with the professional assigned by the Authority in the kebele, have the following duty and responsibilities in regard to the implementation of this Proclamation.

a) Administers the land found in the kebele; cause the decision of land use through participation of public and cooperation of the woreda branch office of the Authority;

b) Facilitates conditions for land distribution by arranging order having received questions of land submitted to it and being helped by the public participation;

ሐ. ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ መመሪያ የቀበሌውን የመሬት ባለይዞታዎችና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች መዝግቦ ይይዛል፤

መ. ማናቸውም የመሬት ድልድል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ፣ አንድን ቦታ ለመንደር ምሥረታ የማዋል ተግባር፣ የወል መሬትን ለግል መጠቀሚያ የማከፋፈልና የአንድን መሬት አገልግሎት የመለወጥ ሥራ እንዲሁም ለህዝብ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር የመሬት ይዞታን ወይም የመጠቀም መብትን የሚያግድ ወይም የሚያሳጣ ማናቸውም ውሣኔ በቀበሌው ሕዝብ ተሣትፎ የተደገፈ መሆኑን ያረጋግጣል።

2. የንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል።

c) Registers and keeps the land holders of the kebele and other persons given land holding certificate according to a directive to be given by the Authority;

d) Ensures any decision that suspends or deprives the right to hold or use land is supported by the participation of the kebeble people, unless it is for any land distribution, holding certificate provision, villagization, distribution of communal land for private use, change of the service of land, as well as public use.

2. The duty and responsibility of the sub-kebele land administration and use committees shall be determined by a regulation.

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

28. መሬትን ለሕዝብ አገልግሎት ስለማስለቀቅ

1. ባለሥልጣኑ የገጠርን መሬት ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ከማንኛውም ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ተገቢውን ካሣ በቅድሚያ በመክፈል ማስለቀቅ ይችላል።

2. ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ይቻል ዘንድ የገጠር መሬት እንዲለቀቅ በባለሥልጣኑ የወረዳ ቅ/መ/ቤት ከመወሰኑ በፊት መሬቱ የሚለቀቅበት ተግባር ከአካባቢው ሕብረተሰብ ልማት ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ሲሆን ጉዳዩ ለቀበሌው ሕዝብ ውይይት ቀርቦ የብዙሃኑን ድጋፍ ማግኘት አለበት።

3. ማናቸውም የወረዳ አስተዳደር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የገጠር መሬት እንዲለቀቅ ሲወሰን ከባለሥልጣኑ የሚያገኘውን

PART SIX

Miscellaneous Provisions

28. Expropriating Land for Public Use

1. The Authority may expropriate rural land from any holder or user for the public service by paying proper compensation in advance.

2. Where the land expropriation activity is directly related with the development of the surrounding society, the case shall be submitted to the kebele people for discussion and get majority vote, therein, before it is decided by the Woreda branch office of the Authority to expropriate land for public service.

3. Where any Woreda Administration decides on the rural land to be expropriated pursuant to sub-Article 1 of

መረጃ መሰረት በማድረግ መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜና የሚከፈለውን የካሣ መጠን ገልጾ ለመሬቱ ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በጽሁፍ ማሣወቅ አለበት:: በካሣው መጠን ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን ለባለሥልጣኑ የማቅረብና የማስመርመር መብት ይኖረዋል::

4. ለሕዝብ አገልግሎት ለሚለቀቅ የገጠር መሬት የሚከፈለው የካሣ መጠን ቀመር በደንብ ይወሰናል::

5. የካሣው ከፋይ መንግስት፣ የግል ድርጅት፣ ሕብረተሰብ ወይም ሌላ አካል ቢሆንም የካሣው መጠን ማስያ ቀመር አንድ አይነት ይሆናል::

29. አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታና ስለባህላዊ ደንቦች ተፈፃሚነት

ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ከመሬት ይዞታ ወይም ከመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማናቸውም ፍትሐብሔር ነክ አለመግባባት ቅድሚያ በሽምግልና ታይቶ በእርቅ እንዲፈታ ጥረት መደረግ አለበት፣

2. የሽማግሌዎች አመራረጥና የእርቁ ድርድር አካሄድ የየአካባቢውን ባህላዊ ስርዓት መሠረት አድርጐ በባለጉዳዮች ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል::

30. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከመሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር ተያይዘው በሌሎች ሕጐች የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች ይህንን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል::

this Article, it shall, based on the infromation from the Authority, notify it in writing to the land holder or user stating the time of expropriation and the amount of compensation to be paid. The party who is aggrieved on the amount of the compensation shall have a right to submit his petition to the Authority and get investigated thereof.

4. The formula of compensation to be paid to the rural land to be expropriated for public service shall be determined by a regulation.

5. Even though, the compensation payer is government, private organization, community or other body, the culculating formula for compensation shall be the same.

29. Conditions of Resolving Dispute and Application of Customary Rules.

Without prejudice to the right of any person to submit pleading to a regular court:

1. Any civil dispute that may arise in connection to land holding or using right shall priorly be seen and resolved in arbitration;

2. The selection of aribitrators and the process of the resolution agreement may be excecuted by the agreement of the parties based on the customary procedures of each surrounding.

30. Transitory Provision

Rights and Obligaions established in other laws in connection to the right of land holding and using, before this proclmation is issued, their application shall continue unless they contravene with this Proclamation.

31. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ኃላፊነት

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ይህንን አዋጅ የጣሰ ወይም አፈፃፀሙን ያሰናከለ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

32. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 46/1992 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡
2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

33. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

34. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር
ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም.

አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

31. Collaboration Obligation and Criminal Responsibility

1. Any person shall have obligation to cooperate with concerned bodies to implement this Proclamation.
2. Any Person who violated or hindered the execution of this proclamation shall be accountable in accordance with provisions of criminal law.

32. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional Rural Land Administration and Usage Determination Proclamation No. 46/2000 is repealed and replaced by this Proclamation.
2. Any Law, regulation, directive or customary practice, inconsistent with this Proclamation shall be inapplicable on matters provided in this Proclamation.

33. Power to issue Regulation and Direcitve

1. The Regional Administrative Council may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.
2. The Authority may issue directives to execute this Proclamation and regulations to be issued pursuant to this Proclamation.

34. Effective Date

This Proclamation shall come to force as of its publication on the Zikre-Hig Gazzette of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 29th day of May 2006

Ayalew Gobezie
President of the Amhara National Region